እነዚህም [የቤርያ ሰዎች] በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፥- ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው እለት እለት መጻህፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ (ሐዋ 17፡ 11)።

ቤርያ

ቁጥር 54

በወረቀት፣ በኢሜይል፣ በፌስቡክ እና በቴሌግራም የሚሰራጭ ወርሃዊ መጽኄት

አዘጋጅ - አበበ መንገሻ (PhD) አድራሻ - ዲላ ከተማ ስ.ቁ. – 0936669160	ኢሜይል - abebe.meng@gmail.com ፌስቡክ - Abebe Mengesha Beshah	ቴሌግራም https://t.me/bereamagazineethiopia (channel) https://t.me/bereamagazine (group)

የእግዚአብሄር መጠሪያዎች

(ክፍል ፩)

ብዙ ሰዎች እግዚአብሄርን ከፈጣሪነቱ፣ ከፈራጅነቱ እና ከወሳኝነቱ ሌላ ባህሪ እንዳለው አያውቁም። በስም ደረጃም እነዚህን በግርድፉ የሚያውቋቸውን ባህሪያት ብቻ የሚወክሉ 'አምላክ' እና 'ፈጣሪ' ከተሰኙት ስሞቹ ውጪ ሌላ መጠሪያዎች (addressing terms) ሊኖሩት እንደሚችሉ አይገምቱም። ነገር ግን እሱ ብዙ ማንም የማይጋራቸው አስደማሚ ባህሪያት እና እነሱን የሚወክሉ ለቁጥር የሚታክቱ ጣፋጭ እና ታላላቅ መጠሪያዎች አሉት። ከእነዚህ መጠሪያዎቹ መካከል ዋና ዋና ማንነቶቹን የሚገልጹትን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

የሰራዊት አምላክ (አሞ 5፡27) - ሰራዊት የተባሉት ቅዱሳን መላእክቱ ናቸው። መላእክት በቁጥር ደረጃ ሊገለጹ የማይችሉ (ራእ 5፡11፤ እብ 12፡12) እንዲሁም እጅግ ሀያላን፣ ቅዱሳን እና ግዙፍ ፍጥረታት ናቸው። ከአመጻቸው የተነሳ ከተመቱት እና ከደከሙት የሰይጣን ሰራዊት ባንጻሩ የእግዚአብሄር ሰራዊት በተፈጠሩበት የሀይል ሙላት የሚገኙ ማንም የማይችላቸው እና በእግዚአብሄር ስልጣን የሚሰሩ ባለማንነቶች ናቸው። እግዚአብሄር ከሰራዊቱ መከከል የተወሰኑትን ለእያንዳንዱ አማኝ ለጥበቃ ይመድባል (ማቴ 18፡10፤ ሀዋ 12፡15)። ስለዚህ እግዚአብሄር 'የሰራዊት አምላክ' ተብሎ መጠራቱ የእነዚህ ሀያላን፣ ቅዱሳን እና ግዙፍ ፍጥረታት አዛዥ እና አሰማሪ መሆኑን ያመለክታል።

ያለና የሚኖር (ዘጸ 3፡14) – 'ያለ' እና 'የሚኖር' የሚሉት ቃላት የአሁን እና የዘላቂ ጊዜ ግሶች መሆናቸው እግዚአብሄር ዱሮም የነበረ፣ አሁንም እየኖረ ያለ እና ወደፊትም መኖሩን የሚቀጥል መሆኑን ያመለክታሉ። የእግዚአብሄር ህይወት ጅማሬ ሊነገር አይችልም (እብ 7፡3)፤ መጨረሻም የለውም። ጊዜ ለእኛ እንጂ ለእሱ አስፈላጊ አይደለም። ዘመን መቁጠር የሚያስፈልገው ጊዜ ለሚያልፍበት እና ተመጥኖ ለተሰጠው ነው፤ እግዚአብሄር ግን አያልፍበትም፤ እንዲሁም መጥኖ የሰጠው አካል የለም። ስለዚህ በደፈናው 'ያለና የሚኖር' ተብሎ ይጠራል።

ኤልሻዳይ (ዘፍ 17፡1፤ ዘሁ 24፡16፤ ዘጸ 6፡3፤ ሩት 1፡20) - ቃሉ እብራይስጥ ሲሆን 'ሁሉን ቻይ' ማለት ነው። እግዚአብሄር የትኛውንም ነገር ለመስራት ከማንነቱ የተለየ የሚይዘው መሳሪያ የለውም፤ የትኛውንም አይነት ኢነርጂ (kinetic, electric, heat, etc) አያወጣም። በማንነቱ ብቻ ሁሉን ያከናውናል። የትኛውንም ስራ ሲሰራ ጊዜ አይጠይቀውም። የሚከተለው ሂደት ወይም ቅደም ተከተል የለውም። መሳሪያ ቢያስፈልገው፣ ኢነርጂ ቢያወጣ፣ ጊዜ ቢፈልግ እና ሂደት ቢኖረው ሁሉን ቻይ ሊባል አይችልም ነበር። 'ኤልሻዳይ' (ሁሉን ቻይ) ያስባለው ይህ የሚሳነው ነገር ያለመኖሩ እና ሲሰራ ምንም ያለመፈለግ ብቃቱ ነው። 'ሁሉን ቻይ' የሚለው ሀረግ ኢዮ 17፡23፣ 25፣ 26 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

የአማልክት አምላክ (መዝ 136:2) - ይህ ስም የእግዚአብሄርን ደረጃ ለመግለጽ የተሰጠ አይደለም። እሱ ከጣኦታት ጋር ይቅርና ከመላእክቱ ጋር እንኳን አይወዳደርም። እንዲሁም አማልክቱ እንኳን የሚያመልኩት እንደሆነ ለመግለጽ የወጣ ስም አይደለም። ምክንያቱም ጣኦታት ግኡዛን ስለሆኑ ማምለክ አይችሉም። ስሙ የሚያመለክተው አምላክነቱ አማልክት የተባሉትን ሁሉ የሚያፈርስ፣ የሚያጠፋ፣ ትርጉም አልባ የሚያደርግ እና የሚውጥ መሆኑን ነው። ለምሳሌ ጸሀይ በሙሉ

ሀይሏ የምታበራበት ቦታ ላይ ሻማ ማብራት ምንም ትርጉም የለውም። ምናልባትም መብራቱ ራሱ ላይታይ ይችላል። በተመሳሳይ እግዚአብሄር ራሱን ሲገልጥ አምላክ ነን የሚሉ ሌሎች ስለአምላክነታቸው ማንም ትዝ አይለውም። ልክ ሻማ መብራትነቷን ለማስመስከር ጨለማ ቦታ መፈለግ እንዳለባት ሁሉ አማልክትም አምላክነታቸው እንዲታወቅላቸው እግዚአብሄር ራሱን ወዳልገለጠባቸው ቦታዎች መሄድ አለባቸው። እሱ በተገለጠበት ሁኔታ ግን የጣኦታት አምላክነት ባዶ ይሆናል።

የጌቶች ጌታ (መዝ 136፡3፤ 1ጢሞ 6፡15) - እሱ በምድር ላይ ጌቶች ነን ከሚሉት በላይ እንደሆነ፣ እነሱም ለእሱ እንደሚገዙ እና ጌትነታቸውን ከእሱ እንደሚቀበሉ የሚያመለክት ስም ነው። በበላይነት ከእሱ ጋር የሚወዳደር ጌታ እንደሌለ ያሳያል። እንዲያውም እሱ 'የጌቶች ጌታ' የተባለው እነሱን ቀድመን ጌታ ስላልናቸው ነው እንጂ የእሱ እና የእነሱ ጌትነት ፈጽሞ አይቀራረብም። እሱ ለጌቶች ጌታቸው ከሆነ ደግሞ ለሌላው ጌታ ላልሆነው ሰውማ እንዴታ! በደምሳሳው ስሙ የሁሉ የበላይ መሆኑን ያመለክታል።

የነገስታት ንጉስ (1ጢሞ 6፡15) - እሱ በምድር ላይ 'ንጉስ ነን' ከሚሉት በላይ እንደሆነ፣ እነሱም ለእሱ እንደሚገዙ እና ንጉስነታቸውን ከእሱ እንደሚቀበሉ የሚያመለክት ስም ነው። በነገስታቱ ላይ ገዢ ከሆነ ደግሞ እነሱ በሚገዙት ነገር ላይ ሁሉ ጭምር ገዥ ነው። ስለዚህ በተጨማሪ ስሙ በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ በእሱ ገዢነት ስር እንደሆነ ያሳያል። ነገስታቱ የሚገዙትን ሁሉ ነጥቆ እነሱን ባዶ ማስቀረት ይችላል። እንዲያውም ሁሉም ነገር ለእነሱ የሚገዛው መጀመሪያ ለእሱ ከተገዛ በኋላ ነው።

አንዳንዶቻችን ልክ እንደምድር የስልጣን ተዋረድ እሱ በምድር ነገስታቱ አማካይነት እንደሚገዛን እንረዳዋለን። እውነቱ እንዲህ አይደለም። መጀመሪያ ለእሱ ከተገዛን በኋላ ነው ለእነሱ የምንገዛው። የእሱ ንጉስነት የሚገለጸው ቤተ መንግስት ውስጥ እና ዙፋን ላይ በመቀመጥ አይደለም። እያንዳንዳችን ውስጥ ሞልቶ እና ሁለመናችንን ወርሶ ይገዛናል። የምድር ነገስታት ሰው እንደመሆናቸው አንድ ከተማ ውስጥ ተቀምጠው አገሩን ይገዛሉ፤ ሁሉ ቦታ ለመድረስ የጊዜ እና የችሎታ ውስንነት አለባቸው። ስለዚህ ሳያዩ እና ሳይሰሙ እነሱ ላይ ማመጽ፣ ሳይደርሱብን ከእነሱ መሸሽ፣ ወደእኛ እንዳይመጡ መንገድ መዝጋት ይቻላል። እግዚአብሄር ላይ ግን የት ሆኖ ይታመጻል? ወዴት ይሸሻል? እሱ የት ሆኖ ነው መንገድ የሚዘጋበት? የነገስታ ንጉስ የተባለው ለዚህ ነው።

የአብርሀም፣ የይስሀቅ፣ የያእቆብ አምላክ (ዘጸ 3፡15) - ይሄኛው ስሙ የሚያሳየው በወዳጆቹ ለመጠራት ያለውን ፍላጎት ሲሆን በወዳጆቹ መጠራት የሚፈልገውም ፍቅሩን ለመግለጽ ነው። ከሰው ጋር ለመያያዝ እና ሰውን ለመቅረብ ያለውን ዝንባሌ ያሳያል። ራሱን አይሰቅልም፤ አይኮራም። እንደሚታወቀው ራሱን የሚሰቅል እና የሚኮራ ኮምፕሌክስ ያለበት ነው። ኮምፕሌክስ ደግሞ ካለመብቃት ጋር ይያያዛል። አምባገነን መሪዎች ራሳቸውን የሚሰቅሉት እና የሚኮሩት ለቦታው እንደማይመጥኑ ውስጣቸው ስለሚነግራቸው እና ያንን ለመሸፈን ስለሚፈልጉ ነው። ስለዚህ ኩራታቸው የውስጣቸውን ባዶነት ማካካሻ ወይም ሚዛን ማስጠበቂያ ሆኖ ያገለግላቸዋል። እግዚአብሄር ግን የሚሸፍነው ባዶነት እና አለመብቃት እንዲሁም የሚጠበቀው ሚዛን የለውም፤ ስለዚህ ወደታች ወርዶ በሚወዱት ሰዎች ስም ለመጠራት አይፈራም።

የዘላለም አምላክ (ዘዳ 33፡27፤ ኢሳ 40፡28፤ ኢሳ 9፡6፤ ዘፍ 21፡33) – ስሙ ጥቅም ላይ የዋለው ከመደገፊያነት እና ከአስተማማኝነት ጋር ተያይዞ ነው። ጊዜ የማይሽረው፣ የማይለወጥ እና አንድ ጊዜ ከያዘ የማይለቅ አምላክ መሆኑን ይገልጻል። እግዚአብሄር በጀመረበት ሀይል፣ ፍቅር፣ ቅርበት እና ቃልኪዳን ለዘላለም ይቀጥላል። ሀይሉ አያልቅም። የሚጀምረው ለመጨረስ ነው። ቃል የሚገባው ለመፈጸም ነው። እንዲሁም የምንለወጠው እኛ እንጂ እሱ አይደለም።

ቅዱሱ (ኢዮ 6፡10፤ ምሳ 9፡10፤ ኢሳ 10፡17) - ይህ ስም ሰዎች እሱን ራሱን ከማወቃቸው እና ቃሉን ከማከበራቸው ጋር ተያይዞ ተጠቅሷል። ከማንም ጋር የማይደመር፣ የማይቀላቀል እና የማይጋጠም፣ ልዩ እና ክቡር አምላክ መሆኑን ያሳያል። እኛ ሰዎችም ይህን ማወቃችን እንድናከብረው እና እንድንፈራው ያደርገናል።

የክብሩ ምንጭ ቅድስናው ነው። ሰው እግዚአብሄርን በዚህ ስም ሲጠራ ራሱን በእሱ ፊት ቆሻሻ መሆኑን በንጽጽር እንዲረዳ፣

ራሱን ዝቅ እንዲያደርግ እና ንስሀ እንዲገባ ያደርገዋል (ኢሳ 6፡3-5)። መላእክት የሚያመልኩት ይህን ስም ደጋግሞ በመጥራት ወይም በማወጅ ነው። ስለዚህ 'ቅዱሱ' የአምልኮ ስሙ ነው ማለት ይቻላል (ራእ 4፡8፤ ኢሳ 6፡3)።

የእስራኤል ቅዱስ (ኢሳ 47:4፤ መዝ 78፡41) - ልዩው እና ከቡሩ እግዚአብሄር የእስራኤል ብርቅ እና ውድ አምላክ እንደሆነ ለማመልከት የተሰጠ ስም ነው። እሱ ራሱ ልዩ ሆኖ ሳለ እነሱን በልዩነት እንደመረጠ እና እነሱ የእሱ ልጆች እንደሆኑ ለማመልከት እንዲሁም በዚህ መመረጣቸው እና ልጅነታቸው መኩራታቸውን እና መጓደዳቸውን ለመግለጽ እስራኤላውያን የሚጠቀሙበት ስም ነው። በተጨማሪ እግዚአብሄር ራሱ ልዩ ሆኖ ሳለ የቀረበውን ሰው ልዩ የሚያደርግ ብርቅ እና ውድ ሀብት መሆኑን ያሳያል።

ልኡል (ዘሁ 24፡16፤ ዳን 4፡17) - ሰው በእግዚአብሄር የበላይነት ሲደመም ያወጣለት ስም ነው። አብዛኞቹ እግዚአብሄርን በዚህ ስም የጠሩ ነገስታት ሲሆኑ የመጀመሪያው ተጠቃሚ የሳሌም ንጉስ ነው። ዳዊት እና ናቡከደነጾርም ደጋግመው ተጠቅመውታል። የበላይ የሆኑ ሰዎች እግዚአብሄር የእነሱም የበላይ እንደሆነ ለመግለጽ ሲፈልጉ እንዲሁም የበላይ ነን ሲሉ ኖረው መጨረሻ እግዚአብሄር ከእነሱ የበለጠ የበላይ እንደሆነ ሲረዱ በዚህ ስም ይጠሩታል። ሰይጣንም እንዲሁ ከእግዚአብሄር ጋር ትከሻውን ሊያለካካ ሲነሳ 'በልኡል እመሰላለሁ' ብሏል (ኢሳ 14፡14)። እውነትም ደግሞ አምላካችን ከፍ ካሉትም በላይ ከፍ ያለ ነው። ከፍ ያለ ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት ሲቀርብ ወይም እግዚአብሄር ሲመጣበት ከፍ እንዳለ አይቆይም፤ ወደእሱ ከፍ ለማለት የፈለገም አይደርስበትም።

ፈጣሪ (መክ 12፡1፤ ኢዮ 36፡3፤ 35፡10) - 'ፈጣሪ' ማለት ጀማሪ እና ምንጭ ማለት ነው። ሰለሞን ይህን ስም የተጠቀመው ጎበዙን ሲመክር ነው። በሀይሉ ከፍተኛውን ደረጃ የደረሰ ሰው ከእሱ ውጭ ሌላ ሀይለኛ አይታየውም። እሱ ራሱ ለዚህ ያበቃው ምንጭ እንዳለው ይዘነጋል። ለዚህ ሰው 'ፈጣሪህን አስብ' ማለቱ 'ማናለብኝ አትሁን፤ ሌላው ቢቀር ወደህይወት ያመጣህ እግዚአብሄር ከበላይህ አለ' እያለው ነው። ማንኛውም ሰው የራሱ ነገር የለውም፤ ሁሉም ነገሩ ከፈጣሪው የተሰጠው ነው። የተፈጠረው ደግሞ ከምንም ነው። ስለዚህ ሰው ከፈጣሪው ከወጣ በራሱ ምንም ነው ማለት ነው። ከፈጣሪው ካለፈ የሚሄደው ወይም የሚሻገረው ወደምንምነት ነው። ምንም የሆነ ነገር መኩራት የለበትም። ስለዚህ 'ፈጣሪ' የሚለው ስም ይህን የጀማሪነት እና የምንጭነት ባህሪውን ይወክላል።

የእስራኤል ብርሃን (ኢሳ 10፡17) - ብርሀን የእሳት አገልግሎት ነው። የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ሲጓዙ በሌሊት የእሳት አምድ እያበራ መንገዳቸውን ያሳያቸው ነበር። ሲሰፍሩ ደግሞ ሰፈራቸው ላይ በማብራት ርስ በርሳቸው እንዲተያዩ እና ስራቸውን እያዩ እንዲሰሩ ያደርጋቸው ነበር። በስጋ ህይወታቸው እንዲህ እያበራ አይናቸውን ሲረዳ በመንፈስ ደግሞ በህጉ እያበራ መንፈሳቸውን ብሩህ ያደርጋል፤ መንፈሳዊ መንገዳቸውን ያሳያቸዋል። ስለዚህ እግዚአብሄር ለእነሱ የመኖር አላማቸውን ግልጽ ያደረገላቸው፣ ከየት እንደተገኙ፣ ህይወታቸው እንዴት እንደሚፈጸም እና እስኪፈጸም ድረስ ምን እያደረጉ መቆየት እንዳለባቸው ያሳወቃቸው ብርሀናቸው ነው። በእነሱ ይጀምር እንጂ ብርሀንነቱ ወደእኛም አልፏል። በእስራኤል ቦታ የእኛን ስም ተክተን 'የ... ብርሀን' ብለን ልንጠራው እንችላለን።

እግዚአብሄር ጽድቃችን (ኤር 23፡6) - 'እግዚአብሄር ጽድቃችን' ማለት የሚተክለን፣ የሚያበቅለን፣ በህይወት እንድንኖር የሚያደርገን፣ የሚቤዠን፣ ወዘተ ማለት ነው። ይህን ስም የያዘው ህዝቡን ከምርኮ አገር (ከባቢሎን) መልሶ በምድራቸው ላይ በተከላቸው ጊዜ ነው። ይህ ጊዜ ህዝቡ የራሳቸውን ትምክህት ጥለው ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሄር ጣልቃ ገብነት ብቻ በሕይወት እንደሚኖሩ የተረዱበት ጊዜ ነበር። በተጨማሪ ስሙ በክርስቶስ ኢየሱስ መስዋእትነት ሁሉ ሰው እንደሚጸድቅ ያሳያል። ምንም ላያተርፍ የእኛን ስራ የሰራልን እና ምንም ላይጠቀም በእኛ ስም ዋጋ ከፍሎ በህይወት ያኖረን ጌታ ይህ ስም ይገባዋል።

የሰማይ አምላክ (ዘፍ 24፡7፤ 2ዜና 36፡23፤ ነህ 2፡20) - ከፍ ያለ፣ በምድር ከሚኖረው ሰው የተለየ እና ከምድር መንግስታት ሁሉ የበላይ የሆነ መንግስት ያለው መሆኑን ያሳያል። እንዲሁም ምድር ላይ የሚከናወኑ ነገሮችን ሁሉ በበላይነት የሚመራ፣ ማንም የማይከለክለው እና የማይፈቅድለት እንዲሁም በራሱ ውሳኔና ፍላጎት በምድር ላይ ያሻውን የሚሰራ መሆኑንም

ያሳያል፡፡ ስለዚህ 'ሰማይ' እንደአማርኛው ምሳሌያዊ አባባል ርቀትን ሳይሆን ከላይ መሆንን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ከላይ ያለ ነገር ደካማም ቢሆን እንኳ ከቦታው አንጻር ከታች ባለው ላይ ይሰለጥናል፡፡ ከላይ የተቀመጠ እቃ በታችኛው ላይ ሙሉ ክብደቱን ይጭንበታል፡፡ በውትድርና ሳይንስ ቀድሞ ተራራ ላይ የሚወጣው የቦታ ከፍታ የሚሰጠው የጦር የበላይነት ስለሚታወቅ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሄር የሰማይ እምላክ የተባለው ሁሌም ከበላይ እንዳለ፣ ሁሌም አዛዥ እንደሆነ እና ሊያሸንፉት የማይችሉት ማንነት እንዳለው ለመግለጽ ነው፡፡

የእብራውያን አምላክ (ዘጸ 3፡18) - 'እብራዊ' የሚለው ቃል የመጣው አቤር ወይም ኤቦር ከሚባለው በአብርሃም ዘር ግንድ ውስጥ ወደኋላ ሲቆጠር ሰባተኛ ትውልድ ላይ ከሚገኝ ሰው ስም ሊሆን እንደሚችል ግምቶች አሉ (ዘፍ 10፡21፣24፣25፤ ሉቃ 3፡35)፡፡ በሂደት ይህ ስም ለአብርሀም ጎሳ መጠሪያ ሆኖ የቀረ ይመስላል፡፡ ስለዚህ 'እብራዊ' ማለት የአብርሃም ዘር አባል ማለት ነው፡፡ ሌሎች ዘሮች ጣኦታትን ለማምለክ ሲመርጡ እብራውያን ግን ሁሉን (ጣኦት የሚሰራበትን ጥሬ እቃ ሳይቀር) የፈጠረውን እግዚአብሄርን ለማምለክ እንደመረጡ ለማመልከት የሚውል ስም ነው (ዮና 1፡9)፡፡ እብራውያን ጥሩ ምርጫ አድርገው በእሱ ለመጠራት ታደሉ፡፡ ቢጠሩበት የሚያኮራ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሄር ለመረጡት ሰዎች ስሙን ሲሰጥ ወይም በእነሱ ሲጠራ ደስ ይለዋል፡፡ ይቀጥላል

የቤርያ ቁ. 53 ጥያቄዎች መልሶች (መላእክት)

1. ሚካኤል (ዳን 10፡13፤ ይሁ 1፡9)፣ ገብርኤል (ዳን 8፡16፤ ሉቃ 1፡19)
2. ኪሩቤል (ህዝ 28፡14)
3. ሚካኤል (ዳን 10፡13)
4. የአምላክ ልጆች (ኢዮ 1፡6፣2፡1)፣ ቅዱሳን (መዝ 89፡5፣7)፣ መናፍስት (እብ 1፡14)፣ ቅዱስ ጠባቂ (ዳን 4፡13፣17፣23)
5. በሰማያት (ገላ 1፡8)

የቤርያ ጥያቄዎች (ጳውሎስ)

1. የጳውሎስ የትውልድ ቦታ ማን ይባላል?
2. ጳውሎስ መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተተ መልእክት የጻፈላቸው ሰዎች እነማናቸው?
3. ሳውል ደማስቆን ለቆ የወጣው ለምንድነው?
4. ጳውሎስና ሲላስ ታስረው ሲዘምሩ መሬት የተናወጠው የት ከተማ ነው?
5. ጳውሎስ የገለጸው ሀዋርያ ማነው?